# <u>በሕዝብ ቁስል ላይ እንጨት የሚሰዱትን በጋራ እንቅጣቸው!</u>

የጫካ ዛፎች እኛስ ምነዋ ተሰብስበን ለችግራችን መፍትሔ ማንፈልግ ብለው ሰፊ ስብሰባ ጠርተው ማነው ጠላታችን ብለው ሲወያዩ አንዱ ፋስ ነው ጠላት ሲል ሌላው ሰው ነው ሲለ አዋቂ ና ብልህ ዛፍ ግን አይ የእኛ ጠላት የራሳችን ጠማማ ነው ብሎ ነገራቸው ይባላል። ዛሬም የራሳችን ጠማሞች በጣም ሕዝብን እየጎዱና ለሀገር ጠላት እየጠቀሙ መሆናቸው በገሀድ እየታየ ነው። ከባዕድ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱ ዜጎች በተለይም ከአሜሪካ የሚመጡት ሕዝብን እያሳዘኑና እያስቆጡም መሆናቸው በቅድሚያ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ ነውና በሕዝብ ቁስል ላይ ጨው መነስነሱ በአስቸኳይ ያቁም አሊያም የሕዝብን ክብር አስጠባቂ ቡድኖች (ሕክአቡ) ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ማስቆም ይኖርባቸዋል ሲሉ ታዛቢዎች ያሳስባሉ።

ከመጀመሪያው እንጀምርና የራሳችን ጠማሞች ያደረሱትን ከፍተኛ ጉዳት እንመርምረው። ዛሬ የኢየሱስ መልዕክተኛ ነኝ ብሎ ሊያሳምነን የሚጥረውና እንደ ባርናባስ እንኳን ፀፀት ሲያሰማ ያልተደመጠው ታምራት ላይኔ፣ በረከት ስምዖን፣ አዲሱ ለገሰና መሰል ከሀዲዎች በኢሕአፓ ላይ ጉዳት አድርሰው ወደ ወያኔ በመፈርጠጥና የጠባብ ብሄረተኛው ቡድን መጋዣ ሆነው ሊያገለግሉ በመወሰን የጠማማነት ምዕራፍን ከፍተዋል። በነዚህ ሽፋን ማለትም ሲጀምሩ ኢትዮጵያዊ ብሎ ኢሕዴን ብሏቸው ና ለስልጣን ሲበቃ ደግሞ የአማራ ናችሁ ብሎ ኤርትራዊው በረከትን ጨምሮ ብአዴን ብሏቸው ሕዝብን ለማደናገር ተጠቀመባቸው። ከወሎ አካባቢ ኢሕዴንን የተቀላቀሉ ብዙዎቹ ቡድኑ የወያኔ መሳሪያ መሆኑን የተረዱ አልነበሩምና ነገር ዓለሙ ምስጢሩ ሲገለጥላቸው ማንጎራጎር ሲጀምሩ ጅብ ከሄደ ሆኖባቸው ለእስርና ለሞት ተዳርገዋል። በሀይል የተበተነውን ቴድሮስ ጦር የተባለውንና በቦምብ የተገደለውን መሪያቸውን ሙሉዓለም ያስታውሷል። ዛሬም ብአዴን መጫወቻ ሆኖ፣ ለወያኔ ጠባቦች የቀትር ጥላና ሕዝብ በስላቅና በጥላቻ እንደሚለው መጋዣና ፌስታል ወይም ኮንዶም--ተጠቅመህብት ጣለው-- ከመሆን አላለፈም። ለዚህም ነው በተደጋጋሚ በወያኔ ላይ አምፁ ወደ ሕዝብ ጎራ ተቀላቀሉ የሚል ጥሪ የሚደረግላቸው። ከኢሕዴን ሌላ ደግሞ የመኮንኖች ማህበር/ድርጅትና ኦሕዴድም እያለ በሌሎች ተጫወተና ኢሕአዴግ የሚል ጭምብልን ወያኔ አጠለቀ። ይህን ማጭበርብር አምነው ኢሕአፓን--ወያኔ ጠላት ነው ስላለ -- በአክራሪነትና በቂመኛነት እየከሰሱ ወያኔ የትግራይ ምሽት እያለ በአሜሪካ መዲናዎች በሚያደርግው የገንዘብ ስብሰባ ምሽት ሱዳን ገዳሪፍ የተሰፋን ሰፌድ ከትግራይ የመጣ እያሉ በጨረታ--ደርግ ባዛር ይለው ዓይነት-- በብዙ መቶ ዶላሮች ሲገዙ የነበሩትንም የራሳችንንም ጠማሞች መጥቀስ እንገደዳለን። ወያኔ ደርግን ተክቶ ዴሞክራሲን የሚያሰፍን ሊሆን አይችልም በሚልም በፍኖተ ዴሞክራሲና በልዩ ልዩ መንገዶችም ይሰጥ የነበረውን ማስጠንቀቂያ ጆሮ አንሰጥ ያሉ ወያኔን በጭብጨባ ተቀብለውታል።

በአሜሪካ አጋፋሪነት የደርግን እጅ መስጠት በሎንዶን እንግሊዝ ለማጠናቀቅ ጉባዔ ተብዬ ሲደረ ግም ኋላ የግድግዳ ላይ ዝንብ ሆንን ያለው የኦነጉ ሌንጮ ለታ ተው ወያኔና ሻዕቢያን አታጅቡ ሲባሉ እምቢ በማለት ያው ድርጅቱ የወያኔ መሳሪያ ሆኖ ለሰፊው ሕዝብ “ የራሳችን ጠማማ” ሆኖ ለወያኔ አገለገለ ። እነ ፕሮፌሰር መሰፍንና እንድርያስ እሸቴ በሲአይኤው ቅጥረኛ በአብዱል አባቦራ አጋፋሪነት ለንደን ድረስ መጥተወና መለስና ኢሳያስንም ተገናኝተው ለሀገር አጥፊው ሂደ ት ድጋፍ ሰጡ። አንደኛው ፕሮፌሰርም እነ መለስን ልጆቼ ብሎ በዚያው በለንደንም ኋላም በአዲስ አበባ ኢሕአፓ መሰል ሀገር ወዳድችን ደም የጠፋቸው ብሎ አወገዘ ። የሽግግር ጉባዔ በተባለውም ቀልድ ተገኝቶ ራሱ ሌንጮ ለታም የወያኔ ድርጅት ጦር የሁሉም የሽግግር ጦር እንዲሆን እጁን አውጥቶ አማራን በጥቅሉ አወግዞ ተፈጠመ ። ለጥቆም የስልጣን ፍርፋሪ ፍሪዳ ሆኖበት--መስሎት የበደኖንም ፍጅት ወልዶ፤ ሌሎች ብሄረሰቦችንም አግልሎ በዚህም በዚያም ለወያኔ ጠቅሞ--የፋስ ብረት መሰኪያ እንጨት ሆኖ-- ያው እንደተጠበቀው በመጨረሻም በወያኔ ሲመታና አባላቱ ሁሉ ሲታፈሱና ለእስር ሲዳረጉ አያ ሌንጮ ደግሞ በሻዕቢያው በኃይሌ መርቆ ሬዎስ አቅራቢነት መለስን ተሰናብቶ  ወያኔ የሰጠውን የመውጫ ቪዛ ተጠቅሞ ከሀገር ወጣ። በገዢው ሀይል ፍቃድ ከሀገር ውጣ ተብሎ የሚወጣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪ በመሆንም እሱና መሰሎቹ አስተዛዛቢ ምሳሌ ሆኑ። ወደ ሽግግሩ ጉባዔ ስንመጣ ደግሞ ወያኔ ሀገር ወዳድ ድርጅቶ ችን--ለምሳሌ በኢዴኃቅ የተሰባሰቡትን-- አግልሎና አግዶ ባለበት ኦነግም ሌሎችም ከወያኔ ጎን ተሰልፈዋል። ከዚያ ሁሉ መንጋ ነጥረው ወጥተው በክህደት ጎዳና አልገባም ያሉት አንድ ያል ተጠበቁ አዛውንት ፕሮፌሰር አሥራት ነበሩ። ሌሎችማ-- ሌንጮ ተባለ ወልደአማኑኤል ዱባለ ፤ በየነ ጴጥሮስ ተባለ አሰፋ ጫቦ ሁሉም ከመቅፅበት የብሄረሰብ ቡድን ወልደው መስርተው ወያኔን በፀረ ኢትዮጵያ ከፋፋይ ዕቅዱ አጅበውታል። የራሳችን የጠማማ ጠማሞች። ተባባሪዎች ለወያኔ፡ በዚህ መልክ በሰፊው ምሳሌዎች እየጠቀሰን መቀጠል እንችላላን። ለወያኔ ድለላ ሰለባ እየሆኑ ከክልል አንድ ባይወለዱም ወይም የወያኔ ድርጅት አባል ባይሆኑም ሀገራቸው ሆዳቸው የሆኑ ዜጎች ለወያኔ እያደሩ ትግልን ጎድተዋል፤ ሀገርን ጎድተዋል።  ለወያኔ ፋስ ጠማማ እንጨት ሆን ው በማገልገል ተመልሰው ወገንን ቆራርጠዋል፤ ፈልጠዋል። ሕዝብም ሁሉን ያዋቃቸዋል።

ነገርን ለማሳጠር በሚል ወደ ዛሬው ጠማሞች ስንመለስ ደግሞ ተሰደው ወይም ዜግነትን ካገኙባ ቸው ባዕድ ሀገሮች ጊዜን ጠብቀው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱት ውስጥ የተወሰኑት ባዕዳን የሚፈ ዕሙትን ብልግናና ንቀት በወገን ላይ እየፈፀሙ ከዚያም አልፎ ወደ መጡበት ሲመለሱ የተገዙ የወያኔ ቅጥረኞች ወይም ወዶ ገባ የወያኔ ቱልቱላዎች እየሆኑ ዜጎችን በማደናገር ዘመቻ መሰማ ራታቸውን ለማወቅ ተችሏል። ወደ ሀገር በለቅሶ ወይም ሰርግ፤ በጉብኝት ወይ ንግድ ምክንያት የሚመለሱት አንዳንዶች ያለፈላቸው ሚጢጢ አላሙዲዎች መስለው በሕዝብ ላይ ሊዘባነኑ ቢሞክሩም አብዛኞቹ በብድር ያገኙትን ዶላር ይዘው በሕዝብ ላይ ሊዘንጡና ሊኩራሩ የሚጥሩ ናቸው። የአሜሪካና አውሮጳ ነጮች ወደ አፍሪቃና እስያ እየተጓዙ ለአቅመ ሔዋንና አቅመ አዳም ባልደረሱ ወንድና ሴት ወጣቶች ላይ እየፈፀሙ ያሉት ብልግናና ግፍ የሚታወቅ ሲሆን

በወገናቸው ላይ ተመሳሳይ በደል በማድረስ አሳፋሪ ታሪክ እያስመዘገቡ ያሉት ደግሞ የራሳችን ጠማሞች መሆናቸው ሊደበቅ የሚችል አይደለም። በአዲስ አበባ በስብሶ ያለው ገዢ መደብና ጭፍሮቹ ከዚህ በፊትም ቢሆን ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱና ከወገባቸው በላይ ራቁት ሆነው መጠጥ አቅራቢ የሆኑ ሴት ልጆች ባሉባቸው ዝግ መጠጥ ቤቶች እንደሚባልጉ በኢን ኤንድ አውት መሸታ ቤት ተይዘው የነበሩት እነ ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴ ምስክር ናቸው። ዛሬ መሰል መሽታ ቤቶቸ በአዲስ አባባ በዝተዋል። በነዚህም ውስጥ ከዚህ ውጪ በደኸዩና አካላቸውን መሸጥ በተገደዱ ህፃናት ሴቶች የሚጫወቱ ከባዕድ ተመላሽ የሆኑ ዜጎች በርክተዋል። የፈረንጅ ዓይነት የወሲብ ቱሪስቶች። ወያኔ አጥፊ ነውና ወጣቱ በጎጂ ልምዶች እንዲጠመድና በአልኮልና አደንዛዥ ዕፅም እንዲጠቃ ይፈልጋል። ነጮች የአሜሪካን መሬት የያዙት የአሜሪካን መሬት ባለ ቤቶችን በመፈፍጨፍ ብቻ ሳይሆን የአልኮል ተገዢ በማድረግ ነበር። አውስትራሊያ የተጋዙ የእንግሊዝ ነጭ ወንጀለኞችም ባለመሬቶቹን ጥቁሮችን--አቦሪጂኒ የሚባሉትን-- ያጠፉት በጭፍ ጨፋና አልኮልንም በማስለመድ ነበር። የአሜሪካ ገዢዎች ጥቁር አሜሪካኖችን በአደንዛዠ ዕፅ ልምድ አሽመድምደው ዛሬም እንደሚገዙ ምስጢር አይደለም። ቅኝ ገዢዎችም አፍሪካን የያዙት የአፍሪካውያንን አንጎል በልዩ ልዩ መንገድ በማዳከም እንደነበር ይታወቃል። ወያኔም ሕዝብን በብሄረሰብና በሀይማኖት እየከፋፋለና በፍጅትም እየመተረ --እያዳከመ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ ዜጋ እንዳይኖር በተለይ ወጣቶችን በቀቢፀ ተስፋ በጎጂ ባህሎችና ልምዶች ወይም ስምሪት አማካይነት ወደ ብኩንነትና ደነዝነት ሊከት ይሁነኝ ብሎ እየሰራ መሆኑ መታወቅ ያለበ ት ነው። ሕዝብ ለሀገሩ ብሎ እንደያምፅ፣ ሰለ ሀገሩም እንዳያስብና እንዳይቆረቆር ለማድረግ በሀይል ብቻ ሳይሆን በድለላምና በአልባሌ ልምዶች ለመተብተብ ሲሞክር ቆይቷል። ከውጭ መጣን ብለው በሕዝብ ላይ የሚዘባነኑና በእህቶቻቸው ላይ የሚጫወቱ ወያኔን እያገዙ መሆናቸው ግልፅ ነው። ወደዱም ጠሉም።

አለን ተመችን ብለው መቶ ብር ለአንድ ምግብ፣ በመቶዎች ብር ለጠርሙስ ውስኪ ሂሳብ የመክ ፈል ችሎታ አለን ብለው፣ ከገዢው ዘረኛ ቡድን ጋር በየዝግ መሸታ ቤቱ ስለተርመስመሱ ወደ ውጭ ሲመለሱ ደግሞ ሀገር በልፅጓል፣ ወያኔን ሕዘብ ተቀብሎታል፣ ትግል ፈላጊ የለም፣ የተቃዋ ሚ ድርጅት መሪዎች ራሳቸው ህንፃ እየገነቡ እጅ ሰጥተዋል፣ ህንፃ መንገዱ ተሰርቷል ተገንብቷ ል፣ አልፎስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲ ምን ሊበጀው ነው ሆዱን ከሞላ እያሉ ( 12 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ መራቡን ሳያነሱ) አፍቅሮ ወያኔን ይሰብካሉ። ወያኔንና ሁኔታውን ከወደዱ ለምን በዚያው መኖርን እንዳልመረጡ መጠየቅ የግድ ነው። አንዳንዶቹ ሳይቀጠሩ በተሰፈኛነትና እበላ ባይነት የወያኔ ሙጀሌና ተምች ሆነው የሕዝብን ስሜት ይቦረብራሉ። እነሱ ወደ ሀገር የመመላለ ስ ዕድል ስላገኙ ሁሉም ዜጋ የዚህ ዕድል ባለቤት የሆነ ይመሰላቸዋል። እነሱ አዲስ አበባ፣ ሶደሬ፣ ወንዶ ገነት፣ አዋሳ ወዘተ ብለው ስለፈነደቁና ስለፈነጩ 85 ሚሊዮን ሕዝብ የደላው ይመስላቸዋ ል። የኔ ብጤው ለማኝ መኪናቸው ጋ እንዳይደርስ በፖሊስ ስለታገደ በሀገሪቷ ድህ የሌለም የሚ መስላቸው ደነዞችም አሉ። የግፍ ግፍ ግን በሕዝበ ላይ ሲቀልዱና ከወያኔ ጋር ሲተቃቀፉ ከቆዩ

በኃላ ተመልሰው የወያኔ ቱልቱላ ወይም አዳናቂ ሆነው የሚያካሂዱት ዘግናኝ ቅስቀሳ ነው፡፡ ይህ በሕዝብ ቁስል ላይ ጨው መነስነስ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ይህን የሚፈፅሙት ግለሰቦች እንደ ወያኔ ሕዝብን የናቁ ናቸው፡፡ በተለይ ከወደ አሜሪካ መጣን ሲሉ ደግሞ እውነትም የአሜሪካንን ሀያልነት የተላበሱ እየመሰላቸው በሕዝብ ላይ የበላይነትንና ንቀትን የሚያሳዩም ሆነዋል፡፡ ይህን ማስቆም ያስፈልጋል፡፡ ብሔራዊ ግዳጅ ነው፡፡

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ይህ በደል በዝምታ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ከዚች ሀገር ተወልደው ግን ህሊናቸውን ገድለው፣ በአሜሪካ አለፈልን ብለው፣በህፃናት ሴቶች ላይና በድሀው ባስተማራቸው ሕዝብ ላይ በደልና ግፍንም የሚፈፅሙትን በዝምታ ማየቱ ማብቃት እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ህፃናትን በገንዘብ ሀይላቸው ተመክተው የሚደፍሩ መከሰስም አለባቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የሕዝብ ክብር አስጠባቂ ቡድኖች (ሕክአቡ) በአዲስ አበባና በሌሎችም ቦታዎች በህቡዕ ተመስርተውና በተቆረቆሩ ዜጎች ተሞልተው አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ያለባቸው፡፡ በዚህ በኩል በአዲስ አበባ በተለይ የተጀመረው ጥረት መደገፍና መስፋፋት አለበት፡፡ በባዕድ ሀገርም ቢሆን ወደ ኢትዮጵታ ተመልሰውና በአፀያፊ ደረጃ ባልገውና ለወያኔ  አጫፋሪ ሆነው ሲያበቁ ሲመለሱ ወያኔን የሚያወድሱና የትግል መንፈስን ሊያደባዩ የሚሰማሩትን ስማቸውን ማጋለጥና ህብረተሰቡ በወያኔ ቅጥረኝነት ደረጃ ፈርጆ ቢያንስ እንዲያገላቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አላሙዲውም፣ በየኮረፍታው በሚሊዮን ብሮች ቪላ የሰራውም ከበርኩ ብሎ በሕዝብ ላይ ሲቀልድ፣ ከውጭ የመጣውም  የቤት ግዢውን ከፍሎ ሳይጨርስ ሕዝባችን ደህይቷልና አላሙዲ ልሁንብህ ብሎ በአላሙዲ ተመሳሳይ አፀያፊ ድርጊት ላይ ሲሰመራ ሁሉም በዝምታ ማየት አይገባም፡፡ በክብር አስጠባቂ ደረጃ መደራጀት ሌላ መሪን ጠያቂ አይደለም--የሀገራችን፣የራሳችንና የታናሽ እህቶቻችን ክብር ነውና በየአካባቢው በመደራጀት ባለጌዎቹን መቅጣትና የነሱ መሰሎችም ከቶም እንዳይመጡ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለነዚህ ህሊና ቢሶች የማስጠንቀቂያ እምቢልታ እነሆ ተነፍቷል፡፡ የሕዝብ ትግል ወደ አዲስ ምዕራፍ እየተሸጋገረ ነው፡፡ መጪው ዓመት ትግል የሚፋፋምበትና አዲስ ምዕራፍም የሚከፈትበት ለመሆኑ ጆሮ ያለው መስማትና አንጎል ያለውም ሊገነዘበው የሚገባ ነው፡፡ ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ እንዲሉ ከወያኔ ጋር ሆነው ሕዝብን ሊያዋርዱና ለወያኔ ጥብቅና ሊቆሙ የተነሱትም መቀወቀጣቸው አይቀርምና ከወዲሁ ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያውን ቢሰሙ የሚሻል ይሆናል፡፡ ነገ ኡኡ ከማለታቸው በፊት የሚሰሙት ጩኸት የተለየ ይሆናልናም ነው፡፡ ሕዝበን የመናቁና እንደ ጠላትና ባዕድ በሕዝብ ላይ መቀለዱና መባለጉ በጋራ ትግላችን ይቆማል፡፡